**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: חורף תשע"ט, 2019

**מספר השאלון: 034284**

**תרגום לאמהרית (6)**

# אזרחות

## לעולים חדשים

**הוראות לנבחן**

א. <u>משך הבחינה</u>: שעתיים וחצי.

ב. <u>מבנה השאלון ומפתח ההערכה</u>:

בשאלון זה שני פרקים.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | (32x2) | — 64 נקודות |
| פרק שני | — | (12x3) | — 36 נקודות |
| סה"כ | | | — 100 נקודות |

ג. <u>חומר עזר מותר בשימוש</u>:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. <u>הוראה מיוחדת</u>:

לפני שתענה, קרא בעיון את ההוראה בראש כל פרק.

כתוב <u>במחברת הבחינה בלבד</u>, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב <u>כטיוטה</u> (ראשי פרקים, חישובים וכדומה).
רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

**የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና**

**የፈተናው ጊዜ፦ የ2019 ዓ.ም. የክረምት ፈተና**

**የፈተናው ቁጥር፦ 034284**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# ሥነ-ዜጋ

## ለአዲስ ገቢዎች

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

א.<u>ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ</u>፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב.<u>የፈተናው መዋቅርና የነጥብ አሰጣጥ</u>፦

ይህ ፈተና ሁለት ምዕራፎች አሉት።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — | (2x32) | — 64 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | — | (3x12) | — 36 ነጥብ |
| በአጠቃላይ | | | — 100 ነጥብ |

ג. <u>ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ</u>፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד.<u>ልዩ መመሪያ</u>፦

ጥያቄውን ከመመለስህ በፊት በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተሰጠውን መመሪያ በጥሞና አንብብ።

ሥራህን በሙሉ <u>በዚህ የፈተና ደብተር ላይ ብቻ</u> ጻፍ። የፈተናውን <u>ረቂቅ</u> (<u>טיוטה</u>)፣ ርዕሶችንና የመሳሰሉትን በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ። በእያንዳንዱ የረቂቅ ገጽ ላይ "ረቂቅ"ብለህ ከላይ ጻፍበት። ማንኛውንም ረቂቅ በሌላ ወረቀት ላይ መጻፍ የፈተናውን ውድቅ መሆን ሊያስከትል ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢቀርቡም ለሁለቱም ጾታዎች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

# ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ (64 ነጥብ)

ከ1-3 ካሉት ጥያቄዎች መካከል ሁለቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 32 ነጥብ)።

**1.** እስራኤል አገር — ይሁዳዊት አገር

ሀ. በህዳር 29፣ 1947 (1947 בנובמבר 29 ,(כ"ט)) የተባበሩት መንግስታት (או"ם) ውሳኔ ምን እንደነበር አብራራ። (8 ነጥብ)

ለ. በነጻነቱ አዋጅ (מגילת העצמאות) ላይ በእስራኤል አገር ውስጥ ለሚኖሩ የአረብ ሕዝቦች እና ለጎረቤት የእስላም አገራት ጥሪ ተደርጓል።
እነዚህን ሁለት ጥሪዎች አብራራ። (12 ነጥብ)

ሐ. በሚከተሉት ሕግጋት በእያንዳንዳቸው የእስራኤል ሃገር ባሕሪይ እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ አብራራ፦

— **የፋሲካ ሕግ (חוק חג המצות)**

— **የራባናት ችሎት ሕግ (חוק בתי הדין הרבניים)**

(12 ነጥብ)

**2.** የሕዝብ የበላይነት እና የዲሞክራሲያዊ ምርጫ መርሆ (עקרון שלטון העם והבחירות הדמוקרטיות)

ሀ. **የሕዝብ የበላይነት (שלטון העם)** መርሆን አብራራ እና ይህም **በዲሞክራሲያዊ ምርጫ** እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን አብራራ። (10 ነጥብ)

ለ. ዲሞክራሲያዊ ምርጫን የሚያሟሉ ሁለት መስፈርቶችን (תנאים) አብራራ። (12 ነጥብ)

ሐ. ለፓርላማ አባልነት ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ውድድር ውድቅ እንዲሆን የሚያደርጉ ሁለት ምክንያቶችን አብራራ። (10 ነጥብ)

**3.** የመንግሥት ባለሥልጣናት (רשויות השלטון)

ሀ. የመንግሥትን ሁለት የሥራ ድርሻዎች አብራራ። (10 ነጥብ)

ለ. የወረዳ ፍርድ ቤት (בית משפט השלום) የሚያከናውናቸውን ሁለት ጉዳዮች አብራራ።
(10 ነጥብ)

ሐ. በእስራኤል አገር የትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ያተኮረ የፓርላማ ምልዓተ ሸንጎው ውይይት አደረገ። በዚህ ውይይት ላይ አንድ የፓርላማ አባል ወደ መንገድ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ቀረበና በአውቶቡስ ማቆሚያዎች የሚቆሙ ብዙ ሰዎች ከአየር ፀባይ ሁኔታ መከላከያ ጉድለት የተነሳ እንደሚሰቃዩ አቤቱታ አሰማ፤ ምክንያቱም በአብዛኛዎቹ ማቆሚያዎች ከዝናብም ሆነ ከፀሐይ የሚከልላቸው ጣራ ስለሌለ ነው። ይህ የፓርላማ አባል የትራንስፖርት አገልግሎት ሚኒስትሩን ይህንን ችግር ቢሮው እንዴት እንደሚፈታው ለፓርላማው አባላት እንዲያስረዳ ጠየቀው።

— ፓርላማው መንግሥትን የሚመረምርበት እና የሚቆጣጠርበትን የሥራ ድርሻ አብራራ።

— ፓርላማው መንግሥትን የሚመረምርበት እና የሚቆጣጠርበት የሥራ ድርሻ በዚህ ክፍል እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ አብራራ።

(12 ነጥብ)

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሁለት (36 ነጥብ)

ከ4-8 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን በአጭር በአጭሩ መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 12 ነጥብ)።

4. **መደበኛ ያልሆኑ የቁጥጥር አሠራሮች** (מנגנוני פיקוח) እና **ክትትል** (ביקורת) ምን እንደሆኑ አብራራ። መደበኛ ላልሆኑት የቁጥጥር አሠራሮችና ክትትል ሁለት ምሳሌዎችን ጥቀስ።

5. በእስራኤል አገር የዜግነት ማግኛ መንገዶች ውስጥ ሁለቱን አብራራ።

6. **በነጻነት የመንቀሳቀስ** (חופש התנועה) መብት ምን እንደሆነ እና **ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ** (חופש הביטוי) መብት ምን እንደሆነ አብራራ።

7. የሚከተሉትን ሁለት ጽንሰ-ሐሳቦች አብራራ፦
   - የሕግ ሉዓላዊነት መርህ (עקרון שלטון העם)
   - ብሄራዊ ማንነት (זהות לאומית)

8. ከፓርላማው አገዛዝ (משטר פרלמנטרי) መለያዎች ውስጥ ሁለቱን አብራራ።

**መልካም ዕድል!**

መብቱ የእስራኤል መንግሥት ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።

**בהצלחה!**

זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך